## እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያዎች**

1. በጁላይ 14 (ቅዳሜ) አጠቃላይ የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም ስለሚኖረን የቤተክርስቲያን አባላት ሁሉ ጠዋት 10 ኤ.ም. ላይ በቤተክርስቲያን ተገናኝተን ጸልየን እንድንወጣ የአገልግሎቱ አስተባባሪዎች በማክበር ይጠይቃሉ።

2. በተለያየ ምክኒያት ወደኋላ የተመለሱ ወገኖችን ለመፈለግና ለመጎብኘት ሽማግሌዎች እቅድ አውጥተው እየተንቀሳቀሱ ስልሆን የምናውቀውና መጎብኘት አለበት የምትሉትን ስም ለወንድም ጌቱ እንድትሰጡ እናሳስባለን።

3. በቤተክርስቲያናችን በለዬ ልዩ አገልግሎት ውስጥ ያላችሁ አገልጋዮች በሙሉ ቀጥሎ በተገለጹት ቀናት ከእሁድ አምልኮ ፕሮግራም በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር ስብሰባ ስለሚኖረን በጊዜ ሰሌዳችሁ መሰረት እንድትገኙ በጌታ ፍቅር እናሳስባለን።

- ⇒ ጁን24/2018 ከጸሎት አገልጋዮች
- ⇒ ጁላይ1 /2018 የቤት ለቤት ህብረት መሪዎች
- ⇒ ጁላይ8/2018 የልጆች አገልግሎት
- ⇒ ጁላይ15/2018 ኮሚኒኬሽን ሚዲያ
- ⇒ ጁላይ22/218 የእህቶች አገልግሎት
- ⇒ ጁን29/2018 ርህራዬ አገልግሎት



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኖሉ?**


**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)


**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10



"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"
(ያዕ. 4:6)


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625


**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**June 24, 2018**

**ሰኔ 17፣ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም አያሌው አስፋው |
| ቃል ............. | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ።” (ኢሳ. 66:2)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመኀ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ግርማ ካሳ

### ከሁሉም የሚበልጠው ማንነት!

*“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።” (2ቆሮ 5፡17)*

ከጥቂት ጊዜ በፊት አልፍሬድ ፖስቴል ስለሚባል አንድ ሰው አነበብኩኝ። ሚስተር ፖስቴል አሁን ቤት-የለሽ (homeless) እና የአእምሮ እመምተኛ ነው። ሚስተር ፖስቴል በጣም የተማረና ትልቅ ስራ የነበረው ሰው ነው። ከታዋቂው የሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ዲግሪ ተቀብሏል። እንዲሁም የኢኮኖሚክስና የአካውንቲንግ ዲግሪዎች አሉት። በጣም ታዋቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር (የአሁኑን የአሜሪካን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ዳኛ ጨምሮ) አብሮ የመማር እድል ነበረው። በጊዜውም ትልቅ ደሞዝ እየተከፈለው ለታወቀ የሕግ ድርጅት ይሰራ ነበር። ነገር ግን በሕይወቱ በገጠመው ሳንካ የተነሳ አሁን በኑሮ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ይገኛል።

የሚስተር ፓስቴልን ህይወት ያነበበ ሁሉ ስለ ማንነቱና ስለ ህይወቱ ትርጉም ማሰቡ አይቀርም። ማንነታችንን ባለን የትምህርት ደረጃ፣ ስራ፣ የገንዘብ ሃብት፣ ማህበራዊ ስፍራ አንጻር የምንመዝን ከሆነ አስተማማኝ መሰረት ላይ አልቆምንም። እንኚህ ሁሉ በቀላሉ የሚሸረሸሩና የሚያልፉ ነገሮች ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ከዘር፣ ከቋንቋ፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከሃብት፣ ከማህበራዊ ስፍራ ... ወዘተ ያለፈ ማንነት ሰጥቶናል። ቃሉ “አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ” (ገላ. 3፡28) ይለናል። እንዲሁም ቃሉ የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ እንደሚል፤ ትምክህት ካስፈለገ የምንመካበት ማንነት በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘነው ማንነት ነው። ይህ ማንነት ነው ምድራዊውን ተሻግሮ ለሰማያዊ ርስት የሚያበቃን። ይህ ማንነት ነው በምድርም ስንኖር የማያቋርጥ የሰላም ምንጭ የሚሆነን። ለዚህ ነው ቃሉ በሌላ በምንም ሳይሆን በጌታ ደስ ይበላችሁ የሚለን። በሌሎችን ነገሮች ለጥቂት ጊዜ ደስ መሰኘት ይቻል ይሆናል። ዘላቂ የውስጥ ሃሴት የሚገኘው ግን በጌታ ላይ ባለን ማንነት ብቻ ነው።

ይህንን ጉዳይ በጥልቀት የተረዱ የእምነት አባቶች ምድራዊውን ነገር ንቀው በተፈጠሩበት ዘላቂ ማንነት ኖሩ። ለዚህ መቼም ከሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚበልጥ አብነት የለንም። እርሱ በምድር ባሉ የክብር መለኪያዎች ተወዳዳሪ አልነበረውም። በትውልድ የቢንያም ወገን ነው፣ እብራዊ ነው፣ ፈሪሳዊ ነው፣ ከገማልያል እግር ስር ቁጭ ብሎ የተማረ የሕግ አዋቂ ነው። ነገር ግን ይህንን ሁሉ ክርስቶስን ከማወቅ ጋር ሲያነጻጽረው እንደ ጉዳትና እንደ ጉድፍ እቆጥረዋለሁ ይላል። (“አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ” ፊሊ. 3፡ 8-9)። የእምነት አባት ሙሴም ስለሚበልጠው በክርስቶስ ስላለው ክብር የግብጽን ባለጠግነትና ክብር እንቢ ብሎ ከወገኖቹ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ። ለምን ቢሉ በአለም (“በግብጽ”) ካለው ማንነት ይልቅ በክርስቶ ያለው ማንነት እጅግ የከበረና የበለጠ እንደሆነ ስለተረዳ ነው። ወገኖቼ፡- የሚስተር ፓስቴልን ሕይወት ስናንብ በእርግጥም በዓለም ያለ ማንነትና ክብር በቅጽበት የሚለወጥና የሚጠፋ ነው፤ ምድራዊና ጊዜያዊም ነው። የሚጸናው በክርስቶስ ያገኘነው ማንነት ነውና በዚያ እንኑር!